

## ጳውሎስ በደማስቆ

- የክርስቲያኖች አሳደጅ የነበረው ሳውል ኢየሱስ ክርስቶስን በደማስቆ መንገድ ላይ አገኘው ። ከተለወጠ በኋላም ልዩ ሰው ሆነ። ክርስቲያኖችን በመግደል የሚታወቀው ይህ ሰው አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ በመሆን ከክርስቲያኖች ጋር ተቀላቀለ። በመጀመሪያ በደማስቆ የነበሩ ክርስቲያኖች ስለእርሱ ምን ማሰብ እንደሚገባቸው እርግጠኞች አልነበሩም። በከተማይቱ ውስጥ በኃይል መስበክ ጀመረ።

- አንዳንድ አይሁዳውያን ለእነርሱ በጣም አደገኛ ሆኖ ስላዩት እርሱን የሚያጠፉበትን መንገድ መፈለግ ጀመሩ። ጳውሎስም ይህ እቅዳቸው ገባው። ጠላቶቹ እርሱ እንዳያመልጣቸው የከተማይቱን መውጫና መግቢያ ሌት ተቀን መጠበቅ ጀመሩ።

- ጳውሎስና ወዳጆቹ ደግሞ ሌላ እርሱ የሚያመልጥበትን ዘዴ ፈጠሩ። እግዚአብሔርም ቢሆን ጳውሎስ በሕይወት እንዲቆይና ወንጌልን እንዲሰብክ ይፈልጋል። እቅዳቸውም ይህን ይመስላል። ጳውሎስን መያዝ የሚችል ትልቅ ቅርጫት አበጁ። ቅርጫቱን በገመድ አስረው ወደምድር ለመልቀቅ ዝግጁዎች ሆኑ። ሲጨልምም ጳውሎስ ቅርጫቱ ውስጥ ገባ። ወዳጆቹም በመስኮት በኩል በገመድ ቅርጫቱን አወረዱት። ጠላቶቹ በሚጠብቁበት የከተማይቱ መግቢያ ጭራሽ መጠቀም አላስፈለገውም። የጠላቶቹ እቅድ ከሸፈ። ጳውሎስም

- ከተማይቱን በሰላም ለቆ ወጣ። ከዚያም በቀጥታ ያመራው ወደኢየሩሳሌም ነበር። በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ግን እውነት ክርስቲያን ሆኗል ብለው ስላላመኑ ፈሩት።

- በርናባስ! መልካሙ በርናባስም ጳውሎስ በእርግጥ የተለወጠ ሰው እንደሆነና እርሱን መፍራት እንደማይገባቸው አስረዳቸው። ከዚያም በዚያ በነበሩት ክርስቲያኖች ተቀባይነትን ካገኘ በኋላ መስበኩን ተያያዘው። ሆኖም ከግሪክ የመጡ አይሁዶች እርሱን ለመግደል ይፈልጉ ነበርና ሁኔታዎች አደገኛ እየሆኑ መጡ።

- ወዳጆቹ መጀመሪያ ወደቂሳሪያ ይዘውት ከሄዱ በኋላ ወደ ተወለደበት ከተማ ወደ ጠርሴስ ላኩት።

*የጳውሎስ በደማስቆ ቆይታ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ስራ በምዕራፍ 9፡ 20 – 25 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com